

# ☙ 6 ❧

# የፓርቲ (የቡድን) መንፈስ

## 6-1

የቆርንቶስ ቤተክርስትያን ምዕመናን መንፈሳዊ ጉዟቸውን ሲጀምሩ የነበራቸው ፍቅርና የኅብረት አቋም በጣም የሚደነቅ ነበር። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ እርስ በእርሳቸው እንዳይስማሙ የሚያደርግ ልዩ መነፈስ በመካከላቸው ስለተፈጠረ የቤተክርስትያኗ አንድነት ተናጋ። እርስ በእርሳቸው በቡድን በቡድን ተከፋፈሉ። የጳውሎስን ትምህርት የሚያንድቁ “እኛ የጳውሎስ ነን” ሲሉ፥ የአጶሎስ የቃላት አጣጣልና አሰባበክ ደስ የሚላቸው ክፍሎች ደግሞ “እኛ የአጶሎስ ነን” አሉ። የቀያፉ (ጴጥሮስ) ህይወት የሚማርካቸው ደግሞ “እኛ የጴጥሮስ ነን” አሉ። እነዚህን ሶስት ቡድን በሙሉ የሚቃወም ሌላ አራተኛ ቡድን ተቋቋመ። እነዚህም “እኛ የጳውሎስም፣ የአጶሎስም፣ የቀያፋም አይደለንም፤…እኛ የክርስቶስ ነን” የሚሉ ነበሩ።

በቲዮሎጂአቸው አራተኛው ቡድን ማለትም “እኛ የክርስቶስ ነን” የሚሉት ልክ የሆኑ ይመስላሉ። ሆኖም ክርስቶስን የወሰዱት ለራሳቸው መጠቀሚያ ብቻ በመሆኑና እነርሱም ገና ከቡድን (ከፓርቲ) መንፈስ ነጻ ባለመሆናቸው ችግር ነበረባቸው። “እኛ ብቻ ልክ ነን…ሌሎቹ ሁሉም ተሳስተዋል” ማለታቸው ብቻ መሠረታቸው በክርስቶስ ላይ ያልታነጸ መሆኑን ያሳያል። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተክርስትያን የገባውን የቡድን (ፓርቲ) መንፍስ ሰምቶ አዘነ። ሞኝነታቸውን ጠባብ የሆነውን አስተሳሰባቸውን ተመልክቶ በእምነታቸው ገና ከህጻናት ያልተሻሉ መሆናቸውን ጻፈላቸው። ጳውሎስ ሆነ አጶሎስ እንዲሁም ቀያፋ ከክርስቶስ የተሰጣቸው አገልጋዮቻቸው መሆናቸውን በመዘንጋት በእነርሱ የሚመኩና የሚታበቱ ሆኑ።

### የቡድን (የፓርቲ) መንፈስ በዘመናት

ችግሩ በቆሮንቶስ ቤተክርስትያን ብቻ ተወስኖ አልቀረም። በየጊዜውና በየስፍራው ይሄ መንፈስ የታይ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። ስማቸው የገነነ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች በአለፉት ዘመናት ተነስተዋል። ከነርሱም መካከል ሉተር፣ ካልቪን፣ ዌስሊ፣ ፊንሊ፣ ሜኖ እንዲሁም ሌሎች ይገኙበታል። እነዚህ ታላላቅ መንፈሳዊ ሰዎች በታሪክ ውስጥ መጥተው ያለፉ ይሁን እንጂ ትምህርታቸውና እምነታቸው በብዙዎች ሕይወት ውስጥ ህያውና ትኩስ ሆኖ ይኖራል። የሚያሳዝነው እነዚህ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እነርሱ ሳያውቁት የቡድን መሪዎች ሆነው አማኞች እርስ በእርስ በቡድን የሚከፋፈሉበት መሆናቸው ነው። “እኔ ሉተራን…እኔ ካልቪኒስት…እኔ ዌስሊያን…እኔ መነናይት ነኝ” በማለት ቡድን መፈጠሩን እነዚህ መሪዎች ቢያውቁ ኖሮ ምን ያህል ልባቸው ያዝን ነበር?

### የቡድን መንፈስ በአጥቢያችን

ይሄ የቡድን መንፈስ ዕንቅፋት የሆነው ትላልቅ መከፋፈል (ዲኖሚኔሽን) የፈጠረ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በትንሹ መንፈሳዊ እንቅስቃሴያችንና ገና በተጀመረው መንፈሳዊ እርምጃችን ላይ ጭምር

ነው። ብዙዎች መልክ ያለው ቋሚ የሆነ ሥራ ሠርተው አልፈዋል። የእኛ ግን ገና አልተጀመረም። በመካከላችንም ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ገና አልተነሱም። ሆኖም ገና ካሁኑ ይሄ የቡድን መንፈስ በመንገዳችን ላይ እየቆመ እርምጃችንን እንዳይገታ እንጠንቀቅ። የኢጥቢያችን ችግር እንደሌላው አይደለም። “እኔ ሉተራን፣ ካልቪኒስ…ዌስሊያን…መነናይት ነኝ” የሚል ችግር የለብንም። እንዲያውም አንዳንዴ ችግራችንን በግልጽ አናውቀውም። ይሄ መንፈስ በኢጥቢያችን እኛ ባለንበት ቤተክርስትያን ውስጥ ውስጡን እናየው እንደሆነው ነው እንጂ ግልጽ ሆኖ አይታይም። አለመታየትም ይሆናል ለማስተካከል አስቸጋሪ የሚሆነው።

## የቡድን መንፈስ እንዴት ይመጣል?

ለቆሮንቶስ ቤተክርስትያን መከፋፈል ምክንያት የሆኑት መሪዎች ናቸው ብለን በድፍረት መናገር ያስቸግረናል። ራሳቸውን በጊዜ ከነበሩት መሪዎች ጋር ማስታከክ የፈለጉ ምዕመናን እንደነበሩ ማየት ግን አያዳግትም።

1ኛ. አብዛኛውን ጊዜ ይሄ የቡድን መንፈስ ሊፈጠርና ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሊከፋፈሉ የሚችሉት የራሳቸውን ገናናነት ለማሳደግ በሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ምክንያት ነው። እነዚህ ሰዎች ሌላውን አሳንሰው ነቅፈውና ትችተው ሲናገሩ ከሥራቸው ያሉት ምዕመናን ይሰማሉ። አስተማሪዎቻቸውና መሪዎቻቸው ስለሆኑ እነርሱ የተናገሩትን ቃል እንደ አምላክ ቃል አድርገው ስለሚቀበሉ፥ በሌላው ላይ ያላቸው ግምትና አስተያየት ዝቅ ያለ ይሆናል። በዚህ ጊዜ አንዳንድ ቡድን ይፈጠርና ሁሉም ራሱ ላለበት የቡድን መሪ ድጋፍ መስጠት ይጀምራል።

2ኛ. ሐዋርያው ጳውሎስ “ሰዎችን ወደ ራሴ ብሰበስብ ወዮልኝ” ይላል። ጳውሎስ ይህን ያለበት ምክንያት በአማኞች መካከል የሚይስከትለውን ችግር ስለተረዳ ነበር። ይህንን ያልተረዱ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ግን ቅርቤ ናቸው የሚሉት ሰዎች የተለየ አስተያየት ቢያደርጉ፥ ሰዎችን ወደ ራሳቸው ሲስቡና የራሳቸ የሆኑትን በዙሪያቸው ማሰለፍ ሲጀርሙ ያኔ ለመከፋፈል ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናሉ።

3ኛ. ሌላው በመሪዎች መንፈሳዊ ትዕቢት ምክንያት የሚመጣ ነው። ውጪያዊ ህይወታቸውን ልዩ አድርገው በማቅረብና ብዙዎች በሥራቸውና እነርሱ በሚያምኑት ትምህርትና አስተያየት ሥር እንዲውሉ ይደርጋሉ። ኃይላቸውን እንጂ እንደሰው ያለባቸውን ድካም አያሳዩም። ከእግዚአብሔር ከራሱ ካልሆነ በቀር ከሰው ትምህርት እንደማያገኙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይናገራሉ። በጠቅላላው ልዩ ፍጡር ሆነው መታየት ይፈልጋሉ። በዚህም ምክንያት በዙሪያቸው ያሉት ምዕመናን አልፎ አልፎ ከክርስቶስ ጋር እኩል አድርገው ያዩአቸዋል። ጳውሎስን የሚያክል ታላቅ መንፈሳዊ ሰው እንኳን ራሱን በቀጥታ ከሰማይ እንደወረደ አድርጎ አላሳየም። ድካሙን፣ ውድቀቱን አልሸሸገም። “ምን ዓይነት ጎስቋላ ሰው ነኝ ከዚህ ከሚሞት ሥጋ ማን ያድነኛል?” ብሎ ሲናገር ትግል እንደነበረበት ሲገልጽ ነበር። መሪዎች በትዕቢት ሕይወታቸው የተነሳ በቀላሉ በሚደግፏቸውና በሌላው መካከል የቡድን መንፈስ እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ያም ለወንጌል መስፋፋት ትልቅ እንቅፋት ይሆናል።

## የቡድን መንፈስ የሚያመጣው ችግር

1ኛ. አንዱ አማኝ ከሌላው አማኝ አንዱ የክርስትያን ክፍል ከሌላው ክፍል ጋር እንዳይገናኝ በመካከ ላቸው ጠላትነት እንዲፈጠር ያደርጋል። ይሄ ብቻ ሳይሆን ከሁለቱም ወገን የሚወረወረው የቃላት ጦርነት ሁለቱንም ወገን የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ ለማያምኑት ሰዎች መልካም ምስክርነት አይሆንም።
2ኛ. እነርሱ ካሉበት ቡድን ውጪ ለሆነ ወይንም ታማኝነቱን እነርሱ ላሉበት ቡድን ካላሳየ ያ ሰው

በእነርሱ አካባቢ ተቀባይነትና ድጋፍ አይሰጠውም። ይሄም የቅሬታ መንፈስ ያሳድርና ግልጽ የሆነ ቅራኔ ይፈጥራል።

3ኛ. አንደኛው ቡድን ሌላው የሚሠራውን ሥራ የሚደግፍና የሚቀበል አይሆንም። በዚህም የእግዚአብሔር ሥራ እንዳይስፋፋ እንቅፋት ይሆናል።

4ኛ. አንዱ ሌላውን የማይቀበለው በመሆኑ አንዱ በሌላው ችሎታና ዕውቀት እንዳይጠቀም ይሆናል። እርሱ መሥራት የማይችለውን ወይንም ሌላው የተሻለ አድርጎ ከሚሠራው ሰው ተቀብሎ መገልገልና በዚያም የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲገለገሉበት እንዳይሆን እንቅፋት ይሆናል።

5ኛ. መንፈሳዊ አገልጋይ ያጠፋል። ትግሉና ሽኩቻው ሲበዛበት ተስፋ ቆርጦ እንዲወጣ ያደርጋል። ያለውን ትግልና ጦርነት ከውጪ ሆኖ ያየ ወደዚያ ውስጥ ለመግባት ይፈራል። በዚህም ምክንያት የሠራተኛ እጥረት ይደርሳል።

## ለችግሩ ምን መፍትሄ ይገኛል?

1ኛ. ችግሩ አብዛኛውን ጊዜ የሚመጣው ከመሪዎች ዘንድ በመሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች በየጊዜው ውስጣዊ ፍልጎታቸው ከምን ላይ እንደተመሠረተ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋቸዋል። አገልግሎታቸው ለራስ ጥቅም፣ ለተሻለ ደረጃ፣ ለተሻለ ደሞዝ፣ ወይንም የበለጠ መንፈሳዊ ስልጣን ለማግኘት እንዲሁም ይበልጥ ለመታወቅ መሆን አለመሆኑን መመርመር ይገባቸዋል።

2ኛ. እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው እንደታማኝነቱና እንደችሎታው ሥራውን አከፋፍሎ ይሰጣል። ስለሆነም አንዱ በሌላው ችሎታና ስጦታ ደስ እንዲለው ይገባል። የሁሉም ድካምና ጥረት የእግዚአብሔ ርን መንግሥት ለማስፋፋት መሆኑን ተገንዝቦ በዚያ ደስ መሰኘት ያስፈልጋል።

3ኛ. ሰው ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም። ስለሆነም በሁሉም ነገር አንድ ዓይነት አስተያየትና አመለካከት እንዲሁም ሚዛን ይኖራል ብሎ መገመትና መጠበቅ ከስህተት ላይ ይጥላል። የማይሰማሙበትን ከማወጅ የሚስማሙበትን አጉልቶ ማሳየት ይበልጥ ይጠቅማል። የእግዚአብሄር ቅልቁ ዓላማው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር ሲሆን፥ ክርስቶስን ከማያከብርና ክብሩን ከሚሻማው ጋር ኅብረት ስለሚኖረው አገልግሎታችንና እንዲሁም ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታችን የክርስቶስን ክብር ብቻ የሚያሳይ ይሁን።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**